# የግንቦት 7 ወታደራዊ ጉዳዮች ቡድን የሕወሓት/ኢሕአዴግ ጀነራል መኮንኖችን ብቃት የገመገመበት ሰነድ ወጣ




የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በ23 ዓመት ጉዞው ያፈራቸው ጄኔራል መኮንኖች ከወታደራዊ አመራር ሳይንስ ትምህርት እና ስልጠና አንፃር

ሲመዘኑ

በግንቦት 7 የወታደራዊ ጉዳዮች ቡድን

የተዘጋጀ ጥናታዊ ፅሁፍ

ክፍል 1

መስከረም 2007 ዓ.ም.

የርዕስ ማውጫ

መግቢያ. 2

1…… የወታደርዊ አመራር ምንነትና ዋና ዋና የአመራር እርከኖች፤. 3

**2…… የወታደራዊ አመራር የስልጠና እርከኖችና ወደ ወታደራዊ የትምህርት አካዳሚዎች መግቢያ መስፈርቶች.. 3**

**2.1. ወታደራዊ አካዳሚ፡ 4**

**2.2. ስታፍ ኮሌጅ.. 4**

**2.3. የአዛዥነት እና የመምሪያ መኮንንነት አካዳሚ… 5**

2.4 የጦር ኋይሎች ዋር ኮሌጅ(Armed Forces War College) **6**

**3…… የመኮንኖች የማዕረግ ዕድገት ሂደት.. 7**

**4…… የጄነራል መኮንንነት የማዕረግ ዕድገት.. 8**

**5…… የቀድሞው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራሮች የሥልጠና ሂደት፤. 10**

**6…… የአሁኑ የሀገር መከላከያ መኮንኖች ከወታደራዊ አመራር ሳይንስና ጥበብ አንፃር. 11**

**7…… ማጠቃለያ. 13**

**8…… አባሪ ሰነድ- ፩ (Annex-1) 15**

**የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በ23 ዓመት ጉዞው ያፈራቸው ጄኔራል መኮንኖች**

**ከወታደራዊ አመራር ሳይንስ ትምህርት እና ስልጠና አንፃር ሲመዘኑ**

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሠራዊት በዘመናዊ መልክ ከተቋቋመበት ከ1927 ጀምሮ እስከ 1983 ዓ/ም ድረስ ጊዜው በሚጠይቀው ወታደራዊ ሳይንስ የተማሩ፣ ዘመናዊ ክህሎትንና ሥንምግባርን የተላበሱ እና በተግባር የተፈተነ ጀግና የምድር ጦር፣ የባህር ኃይልና የአየር ሃይል ሠራዊትና መሪዎችን ለማፍራት የቻለ ነበር:: በሂደቱም ሰራዊቱን ፈታኝ በሆኑ የተለያዩ አውደ ፍልሚያዎች መርተው ለድል ያበቁ ከፍተኛ ወታደራዊ ምሁራንና መኮንኖችን አፍርቶ ማለፉ የሚታወስ ነው:: የማእረግ አሰጣጡም እንዳሁኑ ዘርን መሰረት በማድረግ ሳይሆን የትምህርት ዝግጅትን፣ ወታደራዊ ዲስፕሊንና ሥነምግባርን እንዲሁም በእየእርከኑ ያሳየው ብቃትና ተገቢውን የመቆያ ጊዜ መፈፀሙ ተረጋግጦ፤ ይህንን እንዲያስፈፅም በተዋቀረ ገለልተኛ አካል አቅራቢነት በሀገሪቱ መሪዎች ሹመት ሲሰጥ ኖሯል።



ቀደም ሲል በተገለፀው የማዕረግ እድገት አሰጣጥ ሂደት መሠረት በአጠቃላይ ከ1927 እስከ 1983 ሀገሪቱ 293 ጀኔራሎችን አፍርታ ነበር። በሌላ መልኩ ወያኔ የመንግሥት ሥልጣን ከወሰደበት ከ1983 ጀምሮ ዘርንና ታማኝነትን በቻ መሰረት በማደረግ ለ130 የቀድሞ ሽምቅ ተዋጊ መሪዎቹ ከብርጋዲየር እስከ ሙሉ ጀኔራልነት ማዕረግ አድሎአቸዋል። ከትምህርት ዝግጅት አንፃር 97 በመቶ (126ቱ) የሚሆኑት መደበኛ የወታደራዊ ሳይንስ እውቀትና ከህሎት የሌላቸው ሲሆን ቀሪዎቹ 3 በመቶ የሚሆኑት ተገቢውን የወታደራዊ ሳይንስ የተማሩና በቂ ሙያዊ ክህሎትን ያዳበሩ አራት የቀድሞ ጦር አባላት ብቻ ነበሩ (አሁን ሦስቱ በጡረታ ሲገለሉ አንዱ በፖለቲካ ጉዳይ የተባረሩ ናቸው)። በአጠቃላይ ከነዚህ 130 ጄነራሎች ውስጥ 67ቱ የሆኑ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የሕወሓት አባላት ናቸው።

የዚህ ፅሁፍ አጠቃላይ ዓላማ ባለፉት 23 ዓመታት የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ያፈራቸውን ጀኔራል መኮንኖች ከወታደራዊ ሳይንስና ሙያዊ ክህሎት አንፃር መፈተሽና መገምገም ነው። በዚህም መሰረት ይህን መግቢያ (Introduction) ጨምሮ

1ኛ፡ የወታደራዊ አመራር ምንነት እና ዋና ዋና የጦር አመራር እርከኖች፣

2ኛ፡ የወታደራዊ አመራር የስልጠና እርከኖችና ወደ ወታደራዊ የትምህርት አካዳሚዎች የመግቢያ መስፈርቶች፣

3ኛ፡ የመኮንኖች የማዕረግ እድገት፣

4ኛ፡ የጄኔራል መኮንኖች የማዕረግ እድገት፣

5ኛ፡ የቀድሞው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራሮች ትምህርትና የሥልጠና ሂደት፣

6ኛ፡ አሁን ያለው የጦር ሃይል መኮንኖች የአመራር ሥልጠናና ብቃት፣

7ኛ፡ ማጠቃለያ ሲሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

## 1. የወታደራዊ አመራር ምንነትና ዋና ዋና የአመራር እርከኖች

ወታደራዊ አመራር በተፈጥሮው የሳይንስንና የጥበብን (both Science and Art) ዘርፍ አጣምሮ የያዘና የተከበረ የሙያ መስክ ነው። ይህም በመሆኑ ማንኛውም የጦር ኃይል አባል በአመራር ቦታ ላይ ከመቀመጡ በፊት ዘመኑ የሚጠይቀውን ለየሥልጣን እርከኑ ተገቢ የሆነውን ወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ በመማርና እና ስልጠና በመውሰድ (Military Education and Training) በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ ይጠበቅበታል።

የወታደራዊ አመራር (Military Leadership) ትምህርትና ሙያዊ ስልጠናውም በወታደራዊ የአመራር ንድፈ ሀሳብ ፣ ስትራቴጅና ታክቲክ ትምህርትና የተግባር ሥልጠናን የሚያካትት ሆኖ መደራጀት ይኖርበታል።


በጦር ሀይሎች ውስጥ አመራር የሚሰጡ የአመራር አካላት በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላሉ:: እነሱም:-

1.1. የበታች ሹም (Non Commissioned Officer/NCO)

1.2. መኮንኖች ናቸው (Commissioned Officers) ናቸው::

**የበታች ሹም (Non Commissioned Officer/NCO):-** የሚባሉት ሰራዊቱን በቅርብ የሚቆጣጠሩ፣ የሚያደራጁ፣ የሚያሰለጥኑ፣ የሚመሩትን ሀይል ለውጊያ የሚያዘጋጁ ከፍተኛ ሀላፊነት ያለባቸው የሰራዊቱ የጀርባ አጥንት ሆነው የሚያገለግሉ መሪዎች ናቸው:: በሰራዊቱ ውስጥ በግንባር መስመር ከበላይ አካል የሚሰጣቸውን ትእዛዝ ተቀብለው በተዋረዱ የሚያዙ የሚያዋጉ እና በየትኛውም የሰራዊቱ ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የስታፍ ስራዎችን በኃላፊነት የሚሰሩ ናቸው:: የአመራር ብቃታቸውንም ለማጎልበትም የወታደራዊ

የአመራር ስልጠናም ይወስዳሉ:: በአጠቃላይ የበታች ሹሞች በተዋጊው ሰራዊትና በአመራር መኮንኖች መካከል እንደ ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው::

**መኮንን (Commissioned Officer/CO) ፡-**የሚባለው የወታደራዊ አመራር ጥበብን እና የወታደራዊ ስልት ስልጠናን ወስዶ በምድር ጦር፣ በአየር ሀይል (Pilot Officer) በባህር ኃይል (Ensign) በምክትል መቶ አለቃነት ማዕረግ የተመረቀ(ች) ወይም ከዚያ በላይ እስከ ከፍተኛ ፊልድ ማርሻል ማዕረግ የደረሰ ሁሉ መኮንን ይባላል:: ስልጠና ያልወሰደ ግን መኮንን አይባልም፡፡ አንድ መኮንን በህግ የተሰጠውን ማዕረግና ሀላፊነት ከተቀበለ በኋላ በተመደበበት የጦር ክፍል የሚመራቸውን ክፍሎች ወይም ኃይሎች በትዕዛዝ፣ በማነቃቃት እና በማግባባት ግዳጃቸውን እንዲፈጽሙ ተጽዕኖ የማድረግ ሀላፊነት አለበት::

## 2. የወታደራዊ አመራር የስልጠና እርከኖችና ወደ ወታደራዊ የትምህርት አካዳሚዎች መግቢያ መስፈርቶች

ማንኛውም የሠራዊቱ አባል መኮንን ለመሆን ከዚህ እንደሚከተለው በተዘረዘሩት መሠረታዊ የመኮንኖች የአመራር ሳይንስና ጥበብ ሥልጠና ተቋማትና እርከኖች ውስጥ በመግባት ተገቢውን እውቀትና ክህሎት በማዳበር የሚሰጠውን የተግባርና የንድፈ ኃሳብ መመዘኛ በጥሩ ሁኔታ ማለፍና መመረቅ ይኖርበታል።የወታደራዊ አመራር የስልጠና እርከኖችም የሚከተሉት ናቸው፡-

2.1. የእጩ መኮንኖች መሰረታዊ የአመራር ስልጠና

2.2. የስታፍ ኮሌጅ

2.3. የአዛዥነትና የመምሪያ መኮንንነት

2.4. የጦር ኮሌጅ ናቸው::

### 2.1. ወታደራዊ አካዳሚ፡

ይህ አካዳሚ የዕጩ መኮንኖች ማሰልጠኛ ሲሆን ተቋሙ እንደ የሀገሩ እና አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በጦር ኃይሎች ውስጥ እጩ መኮንኖችን መልምሎ ወታደራዊ የአመራር ጥበብና ሳይንስ በማስተማር ሠራዊቱን ለመምራት እና ለማገልገል የሚያዘጋጅና አጥጋቢ ውጤት ያመጡትን አስመርቆ ወደ ተለያዩ የሠራዊቱ ክፍሎች እንዲሰማሩ የሚያስችል ተቋም ነው፡፡ ወደ አካዳሚው የእጩ መኮንነት ኮርስ መግባት የሚቻለው ከዚህ የሚከተሉት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

ሀ. እድሜያቸው 17 እስከ 23 ዓመት የሆነ (የሆነች)፣

ለ. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በሚገባ ያጠናቀቁ ሆነው በትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት ከክፍል ወደ ክፍል በሚሸጋገሩበት ጊዜ በክፍል ውጤት ደረጃቸው ከ1ኛ እስከ 5ኛ የወጡ፣

ሐ. ከፍተኛ የትምህርት ተቋም/ኮሌጅ በዲፕሎማ በጥሩ ሁኔታ የተመረቁ፣

መ. ከዩኒቨርሲቲ የአንደኛ ወይም የሁለተኛ ዓመት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ፣

ሠ. ከሰራዊቱ ውስጥ ከበታች ሹማምንት ውሰጥ ፲ አለቃ እና ከዛ በላይ ሆነው በአካዳሚ እውቀታቸውና ወታደራዊ አመራር ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው፡;

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልተው የተመለመሉ እጩ መኮንኖችም በአካዳሚው ውስጥ ከሦስት እስከ አራት ዓመት ለሚሆን ጊዜ የአካዳሚክ፣ የወታደራዊ ስልቶች፣ መሰረታዊ የአመራር ሳይንስና ጥበብ፣ የአካል ብቃት፣ የሞራል እና የስነ ምግባር ትምህርቶችና የተግባር ሥልጠናዎችን በመማር የብቃት መመዘኛ ፈተናዎችን በአጥጋቢ ሁኔታ ሲያሟሉ እንዲመረቁ ይደረጋሉ፡፡ የብቃት ደረጃ የሚለካባቸው መስፈርቶችም፡- የአካዳሚ ብቃት 55% ፤ የወታደራዊ ብቃት 30% እና የአካል ጥንካሬና የአትሌቲክስ ብቃት 15% ይይዛሉ፡፡ ኮርሱን ሲጨርሱና በምዘናው አጥጋቢ ውጤት ሲያመጡ በመጀመሪ ደረጃ የሳይንስ (Bachelor of Science / B.Sc) ዲግሪና በምክትል መቶ አለቃነት ማዕረግ ይመረቃሉ፡፡ በአጠቃላይ አካዳሚው ተመራቂ መኮንኖችን በቆይታቸው ወቅት በሠራዊቱ ውስጥ የአንድ የመቶ ጦር (ኃይል) ለማዘዝ የሚያስችላቸውን ወታደራዊ የአመራር ጥበብ ትምህርት እና የአካዳሚክስ እውቀት በሚገባ ታጥቀው እንዲወጡና በብቃት እንዲያገለግላሉ ያስችላቸዋል፡፡

## 2.2. ስታፍ ኮሌጅ

ስታፍ ኮሌጅ ማለት የመካከለኛ መኮንኖች የአመራር ሳይንስና ጥበብ የሚማሩበት ተቋም ነው፡፡ በዚህ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የወታደራዊ አመራር ትምህርት፣ የአስተዳደር እና የስታፍ መምሪያ መኮንንነት ተግባር እና ሀላፊነት፣ የወታደራዊ ሥነምግባር፣ የወታደራዊ ሙያ ፖሊሲ እና የአካል ብቃት ትምህርቶች ይሰጣሉ፡፡ በኮሌጁም ውስጥ በሁለት ደረጃ የተከፈሉ ሥልጠናዎች ማለትም ጁኒየር እና ሲኒየር ኮርሶች ይሰጣሉ። ወደ እዚህ ኮሌጁ ለመግባት የግድ ማሟላት የሚገባቸው መሰፈርቶች በሲኒየር የሻምበልነት ወይም በሻለቃነት ማዕረግ ሰራዊቱ ውስጥ ግዳጅን መወጣትና ማገልገል ናቸው፡፡

***ሀ. የጁኒየር ኮርስ፡*** ይህ ኮርስ ሲኒየር የሆኑና የሻምበል ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች ገብተው የሚማሩበት ፕሮግራም ነው። የሚሰጠውም የኮርስ ይዘት የወታደራዊ አመራር እና የስታፍ መኮንንነት ተግባራትን፣ የወታደራዊ ሥልቶችን እና የአካል ብቃት ሥልጠናን ያካተተ ነው፡፡ ኮርሱም የሚፈጀው ጊዜ ሃያ ሳምንት ሲሆን ኮርሱንም ሲጨርሱ የሻምበል አዛዥ ወይም በሻለቃ መምሪያ ውስጥ በስታፍ መኮንንነት የኃላፊነት ቦታ ይሰራሉ፡፡

**ለ. የሲኒየር ኮርስ፡** ይህ ኮርስ ጁኒየር የሆኑ የሻለቃ ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች የሚሳተፉበት ኮርስ ነው፡፡ ትምህርትና የሥልጠናውም ይዘት ወታደራዊ የአመራር ሳይንስና ጥበብ፣ የወታደራዊ ሥልጠናዎች፣ የአስተዳደር እና የሎጂስቲክ ትምህርቶች፣ የስታፍ መኮንንነት ተግባር እና ኋላፊነት እና የአካል ብቃት ሥልጠናዎችን ያካትታል፡፡ የኮርሱም የቆይታ ጊዜ አንድ ዓመት ነው፡፡

መኮንኖቹ ኮርሱን ሲጨርሱ የሻለቃ አዛዥ ወይም በብርጌድ መምሪያ ውስጥ የስታፍ መኮንን ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በአጠቃላይ የስታፍ ኮሌጅ ሥልጠና የጨረሱ መኮንኖች የሚሰጣቸው የትምህርት ማስረጃ ዲፕሎማ ነው፡፡

## 2.3. የአዛዥነት እና የመምሪያ መኮንንነት አካዳሚ

ይህ አካዳሚ ሲኒየር ሻለቃዎች እና ሌ/ኮሌኔሎች በመቀበል ለከፍተኛ አመራር ሰጭነት የሚያስተምር ተቋም ነው፡፡ ወደ አካዳሚው የመግቢያ መስፈርቱም የጁኒየር እና የሲኒየር ስታፍ ኮሌጅ ኮርሱን ካጠናቀቁ መኮንኖች ውስጥ በአመራር ሰጭነታቸውና በስነምግባራቸው የሚመረጡ ይሆናል፡፡ ኮርሱም በዋነኝነት በወታደራዊ የአመራር ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ በወታደራዊ ታሪክ፣ በወታደራዊ ሥልቶች፣ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እና የአካል ብቃት ትምህርቶች ያተኮረ ሆኖ ከ10-12 ወራት የሚሆን ጊዜን ይፈጃል፡፡ ኮርሱን አጠናቅቆ ለመጨረስ እንዲያስችላቸው የመመረቂያ ጥናታዊ ፅሁፎችን አዘጋጅቶ ማቅረብና አጥጋቢ ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ መኮንኖቹም ትምህርታቸውን ሲጨርሱ በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ የማስተርስ (Master of Military Arts and Sciences) ዲግሪ ይሰጣቸዋል፡፡ ከሥልጠናው በኋላም የሥራ ኃላፊነታቸውም የሻለቃ ወይም የብርጌድ አዛዥ ወይም በክ/ጦር (በዕዝ) መምሪያ ውስጥ የመምሪያ መኮንን በመሆን ያገለግላሉ፡፡ መኮንኖቹ ከተመረቁና በያዙት ማዕረግ የተወሰነ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በዚሁ አካዳሚ ውስጥ እንደገና ሁለት ኮርሶችን ይወስዳሉ፡፡

እነዚህም፡-

ሀ/ ከፍተኛ ወታደራዊ ጥናትና

ለ/ የዕዝ አዛዥነት

እነዚህ ኮርሶች በዋናነት የሚያተኩሩት በወታደራዊ ስትራቴትጂክ ጉዳዮች እና የዕዝ አዛዥነት ንድፈ ሀሳብ ላይ ነው፡፡ ኮርሱንም ሲጨርሱ የወታደራዊ ዕቅድ ነዳፊዎች (Strategic Military Planners) ሆነው ይመደባሉ፡፡

## 2.4 የጦር ኃይሎች የጦር ኮሌጅ (Armed Forces War College)

ይህ ተቋም በወታደራዊ የሥልጠና እርከን ውስጥ የመጨረሻው የስትራቴጂክ አመራር ሥልጠና (Strategic Leadership Training) የሚሰጥበት የጥናት እና የምርምር ማዕከል ነው፡፡ በዚህ ተቋም ውስጥ የኮርሱ ተሳታፊዎች የሚሆኑት በምድር ኃይል፣ በአየር ኃይል፣ እና በባህር ኃይል ውስጥ ስትራቴጂክ አመራር (Strategic Level Leaders) እየሰጡ ከሚገኙት እና ከከፍተኛ ስቪል የመንግስት ባለስልጣናት ውስጥ ቢያንስ ማስተርስ ዲግሪ ያላቸውን ፖሊሲና እስትራቴጂ አውጪ ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉትን በመቀበል ለከፍተኛ የሥልጣን ቦታ እና ሀላፊነት የሚያዘጋጅ የፖሊሲ እና የስትራቴጂ ጥናት እና ምርምር ተቋም ነው፡፡

እንደ ተለያዩ ሀገሮች ተጨባጭ ሁኔታ በጦር ሀይሎቻቸው ውስጥ እራሳቸውን የቻሉ የምድር ሀይል የጦር ኮሌጅ፣ የአየር ሀይል የጦር ኮሌጅ እና የባህር ሀይል የጦር ኮሌጅ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ሆኖም በወታደራዊ የሥልጠና እርከን መሰረት ሁሉም ሀይሎች አመራር መኮንኖቻቸውን በየራሳቸው የጦር ኮሌጅ ትምህርታቸውን ካስጨረሱ በኋላ ወደ ዋናው የጦር ኃይሎች የጦር ኮሌጅ ገብተው እንዲሠለጥኑ ያደርጋሉ፡፡

ወደ ጦር ኋይሎች የጦር ኮሌጅ ለመግባት በቅድሚያ መሟላት ያለበት፡-

1. የአዛዥነትና የመምሪያ መኮንንነት ኮርስን መጨረስ፣
2. በጦር ኃሎች የጦር ኮሌጅ የሚሰጠውን ኮርስ መጨረስ፣
3. በሠራዊቱ ውስጥ በአመራር ሰጭነት ከ 22 ዓመት በላይ ማገለገል፣
4. በወታደራዊ ሥነምግባር ምንም ችግር የሌለበትና፣
5. የአካል ብቃቱ በሀኪም የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡;

ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ወደ ጦር ኋይሎች የጦር ኮሌጅ የሚገቡት ለብርጋዲየር ጄኔራልነት የሚታጩ ስለሆነ በምድር ኃይል በሙሉ ኮሎኔል ማዕረግ በአየር ኋይል ተመጣጣኝ በሆነው Group Captain እና በባህር ሀይል ደግሞ ካፒቴን (Captain) በአጠቃላይ ሁሉም በኮሎኔል ማዕረግ ደረጃ ሆነው በማገልገል ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

የኮርሱም ተሳታፊዎች መጠንም 75 በመቶ ከጦር ኋይሎች ከሦስቱም ኃይሎች ተመጣጣኝ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ መኮንኖችን እና 25 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከሲቪል የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከሀገር ውስጥ ጉዳይ፣ (በአሁኑ የፌደራል ጉዳዮች) እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ተመርጠው እንዲሣተፉ ይደረጋል፡፡ ኮርሱም የሚያተኩርባቸው ርዕሰ ጉዳዮችም የስታራቴጂክ አመራር ጥበብ፣ የብሔራዊ ደህንነት ስትራቴጂ ጥናት (National Security Strategy)፣ የግጭት ማስወገድ ጥናቶች (Conflic Resolution Research)፣ የህብረት ጥምር ውጊያ ፍልስፍና (War Games) እንዲሁም የጥናት እና ምርምር ንድፈ ሀሳብ ትምህርት የሚሰጥበት ማዕከል ነው፡፡ መኮንኖቹ ትምህርቱን ሲጨርሱም በስትራቴጂ ጥናት የማስተርስ ዲግሪ (Master Degree in Strategic Studies) ደረጃ ይመረቃሉ፡፡ በጦር ኋይሎች ውስጥም የኮር ወይም የዕዝ አዛዥ ወይም በሀገር መከላከያ ጠቅላይ መምሪያ የመምሪያ መኮንነት የሥራ ኋላፊ ሆነው እንዲሠሩ ይደረጋል። በጦር ሀይሎች የጦር ኮሌጅ ውስጥ ትምህርታቸውን ጨርሰው የተመረቁ መኮንኖች ምንም አይነት የዲሲፒሊን ችግር ሪከርድ የሌለባቸው ከሆነ በቀጥታ የብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ ይሰጣቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተቀመጠው መሠረታዊ የሆነው የመኮንኖች የአመራር ጥበብ ስልጠና ሂደት ከዕጩ መኮንነት ኮርስ እስከ ጦር ኮሌጅ የሚዘልቅና መንገዱም ሌላ አቋራጭ የሌለው ረዥም እና አስቸጋሪ ውጣ ውረድ የበዛበት መሆኑን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ይህንን ረጅም መንገድ ያለፉ መኮንኖች ሁሉ የተሰጣቸውን ግዳጅ በብቃት የተወጡ ስለመሆናቸው ያለፉት ታላላቅ አውደ ውጊያዎች(በምስራቅና በሰሜን ኢተዮጵያ) ምስክርና ማስረጃዎች ናቸው፡፡

## 3. የመኮንኖች የማዕረግ ዕድገት ሂደት

የመኮንኖች የማዕረግ ዕድገት መነሻውም ሆነ መድረሻው ወታደራዊ ትምህርትና ሥልጠና ነው፡፡ የወታደራዊ አመራር ሳይንስ ጥበብ ደግሞ ለመኮንነት ማዕረግና ዕድገት የማዕዘን መሰረተ ድንጋይ ሲሆን በአጠቃላይ የመኮንነት የማዕረግ ዕድገት በሥልጠና እየታገዘ የሚከናወን ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው፡፡ መኮንን ለመሆን በቅድሚያ የዕጩ መኮንንነት ኮርስ ወስዶ በሚገባ ማጠናቀቅን ይጠይቃል። የአንድ መኮንን የመጀመሪያው ማዕረግም በምድር ሀይል ምክትል መቶ አለቃ (Second Lieutenant) በአየር ሀይል ፓይለት መኮንን (Pilot Officer) በባህር ሀይል ደግሞ ኢንሳይን (EnSign ) ይባላል፡፡ ምክትል መቶ አለቃ ሆኖ የተመረቀ መኮንን ወደ ሚቀጥለው የማዕረግ ዕድገት ለማለፍ የግል ሪፖርቱ ተገምግሞ ምንም ዓይነት የዲሲፒሊን ችግር ከሌለበት በምድር ሀይል ሙሉ መቶ አለቃ (Lieutenant) በአየር ሀይል በራሪ መኮንን (Flying Officer) በባህር ሀይል ምክትል ሊዩተናንት (Sub – Lieutenant) ይሆናል ፡፡ በሙሉ መቶ አለቃ ማዕረግ ደግሞ አምስት ዓመት ካገለገለ በኋላ የሻምበልነት ማዕረግ ያገኛል፤ በሻምበል ማዕረግ ደግሞ አራት ዓመት ማገልገል አለበት፡፡ በአራት ዓመት የቆይታ ወቅትም የስታፍ ኮሌጅ ኮርሱን ካጠናቀቀና በቆይታ ጊዜ ውስጥ ያስመዘገበው የወታደራዊ ዲሲፒሊን እና የሙያ ብቃቱ ተረጋግጦ በበቂ ሁኔታ ከአለፈ የሻለቃነት ማዕረግ ዕድገት ይሰጠዋል፡፡

በሻለቃ ማዕረግ የቆይታ ጊዜ አራት ዓመት ሲሆን በአራት ዓመት ውስጥም የአዛዥነትና የመምሪያ መኮንንነት ኮርስ ይወስዳል፡፡ የሻለቃ የማዕረግ ቆይታውን ሲጨርስ በሠራዊቱ ሕገ ደንብ መሰረት በዋንኛነት የወታደራዊ ዲሲፒሊኑ፣ የአመራር ብቃቱ፣ በተዋረድ የወሰደው የወታደራዊ አመራር ስልጠና እና በቆይታው ጊዜ ባስመዘገበው ሪፖርት ተመስርቶ ይገመገምና ወደ ሚቀጥለው የማዕረግ ዕድገት የሚያልፍ ከሆነ የሌ/ኮሎኔል ማዕረግ ይሰጠዋል፡፡ የሌ/ኮሎኔል ማዕረግ ቆይታ አራት ዓመት ሲሆን በአራት ዓመት ቆይታው ወቅት የሚወስዳቸው ኮርሶች የአዛዥነትና የመምሪያ መኮንንነት ኮርስ እንዲሁም የምድር ኃይል ወይም የአየር ኃይል የጦር ኮሌጅ የአመራር ጥበብ ሥልጠናን ወስዶ ከጨረሰና በቆይታ ጊዜውም ውስጥ ምንም ዓይነት የዲሲፒሊን ችግር ከሌለበት የሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ከሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ ወደ ቀጣዩ ማዕረግ ለማደግ ቢያንስ የአራት ዓመት የቆይታ ጊዜ ያስፈልጋል ፡፡ በአራት ዓመት የቆይታ ጊዜ ውስጥም የጦር ኃይሎች የጦር ኮሌጅ በመግባት የስትራቴጂክ የአመራር ጥበብ መውሰደና መመረቅ ይኖርበታል:: ኮርሱንም ከጨረሰ በኋላ በቀጥታ የወሰደው የአመራር ሥልጠና እርከን፣ የአመራር ብቃቱ እና አጠቃላይ የ22 ዓመት የአገልግሎት የቆይታ ሪፖርት ተገምግሞ ከአለፈ የብ/ጄነራልነት የማዕረግ ዕድገት ይሰጠዋል፡፡ ትክክለኛ የመኮንኖች የማዕረግ እድገት አሰጣጥ ሂደትና ይዘት ከላይ በተጠቀሰው የትምህርት፣ የስልጠና፣ የሥነምግባር አፈፃፀም ግምገማ ውጤትን መሠረት ባደረገ መንገድ የሚከናወነው ብቻ ነው፡፡

## 4. የጄነራል መኮንንነት የማዕረግ ዕድገት

የጄነራል የመኮንነት የማዕረግ ዕድገት መሰረታዊ የትምህርትና ሥልጠና ዝግጁነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ ያህል በአሜሪካ የጦር ኃይሎች ውስጥ የጄነራልነት ሹመት በፕሬዘዳንቱ አቅራቢነት በህግ መወሰኛው ምክር ቤት ይጸድቃል፡፡ በሌሎች ሀገሮች ግን የጄነራልነት ሹመት የሚካሄደው በመከላከያ ሚኒስቴር በሚቋቋመው የማዕረግ ዕድገት ቦርድ ወይም በመከላከያ ካውንስል በተቋቋመው በሰራዊቱ ህገ ደንብ መሠረት መመዘኛውን ያሟሉ ተመርጠው ለሀገሪቷ ፕሬዘዳንት ቀርቦ ይጸድቃል፡፡

የጄነራል መኮንንነት ማዕረግ ከፍተኛው የወታደራዊ ማዕረግ እርከን ሲሆን በጦር ኃይሎች ( በምድር ኃይል፣ በአየር ኃይል እና በባህር ኃይል) ከፍተኛውን ኃይል የሚመሩ ወይም የሚያዙ፣ ሠራዊቱን የሚያደራጁ፣ የሠራዊቱን ህግ ደንብ የሚያወጡ፣ ሠራዊቱ የሚዋጋበትን የጦርነት ህግ እና ሠራዊቱ የሚሰለጥንበትን የሥልጠና ፖሊሲ፣ የወታደራዊ ዶክትሪን እና ስትራቴጂ የሚቀርጹ፤ በአካዳሚም ሆነ በወታደራዊ ሳይንስ እና ጥበብ የተካኑ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው የጦር ኃየሎች ጄነራል መኮንኖች ናቸው፡፡

*ሰንጠረዥ-ሀ፡- የጄነራል መኮንኖች የማዕረግ አጠራር በተለያዩ የጦር ኃይል ክፍሎች*

| ተ.ቁ | በምድረ ኃይል | በአየር ኃይል | በባህር ኃይል |
|---|---|---|---|
| 1 | Brigadier General | Air Commodore | Commodore |
| 2 | Major General | Air Vice Marshal | Rear Admiral |
| 3 | Lieutenant General | Air Marshal | Vice Admiral |
| 4 | Full General | Air Chief Marshal | Admiral |
| 5 | Marshal or Field Marshal | Marshal Air Forces | Admiral of the fleet |

**ሀ. ብርጋዴር ጄነራል፡** ይህ ማዕረግ ከሙሉ ኮሎኔል ቀጥሎ የሚሰጥ ሲሆን የጄነራል መኮንኖች የመጀመሪያ ማዕረግ ነው፡፡ ከሙሉ ኮሎኔልነት ወደ ብርጋዴር ጄነራልነት ለመሸጋገር መመዘኛዎቹ፡

**1)** በኮሎኔልነት ማዕረግ የአገልግሎት ዘመን፣

**2)** የወታደራዊ የአመራር ጥበብ በተዋረድ የወሰደ፣

**3)** በአገልግሎት ዘመኑ ያሳየው ዲሲፕሊን፣

**4)** የወታደራዊ አመራር ብቃቱ እና ልምዱ፣

**5)** በብ/ጄነራልነት ማዕረግ ሊሰራበት የሚችልበት የሥራ ቦታ ክፍት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ብርጋዲር ጄነራል ማዕረግ ያለው መኮንን በጦር ኃይሎች የብርጌድ ወይም የክፍለ ጦሩ አዛዥ እንዲሁም የኮር እስታፍ ይሆናል፡፡ በያዘው ማዕረግም ከሁለት እስከ አራት ዓመት ያገለግላል፤ የጡረታ ጊዜውም በያዘው ማዕረግ አምስት ዓመት ከቆየና 30 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ከሞላው ጡረታ ይወጣል፡፡ የጡረታ የዕድሜ ጣራውም 62 ዓመት ይሆናል፡፡

**ለ.ሜጀር ጄነራል፡** ይህ ማዕረግ ከብ/ጀኔራል ማዕረግ ቀጥሎ ያለ ባለ ሁለት ኮከብ ማዕረግ ነው፡፡ ከብ/ጀ ወደ ሜ/ጀኔራል የማዕረግ ዕድገት ለመሸጋገር በቅድሚያ ፡-

- ክፍት የስራቦታ መኖሩ (Number of Open Positions) ፣
- በአመራር ብቃት የፈጸማቸው ግዳጆች፣
- በወታደራዊ ሥነ ምግባር ምንም ችግር የሌለበት፣
- የአመራር የሥልጠና እርከን በተዋረድ የወሰደ፣
- የአገልግሎት የቆይታ ጊዜውን (Years of Services) የጨረሰ መሆኑ መታየት ይኖርበታል።

መኮንኑ ሜ/ጀኔራል ከሆነ በኋላ የሥራ ኃላፊነቱም የክፍለ ጦር ወይም የዕዝ አዛዥ ወይም በጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የመምሪያ መኮንን ሆኖ መሥራት ነው፡፡ በያዘው ማዕረግም እስከ አምስት ዓመት ከአገለገለ በኋላ ወይም 35 ዓመት በጦር ኃይሎች ውስጥ አገልግሎት ከሰጠ ጡረታ ይወጣል፡፡ የጡረታ ዕድሜውም 62 ዓመት ነው፡፡ ከዕድሜው ጣራ ውጭ በተለየ ሁኔታ በሥራ አስፈላጊነት አራት ዓመት በተጨማሪ የመስራት አማራጭ አለው፡፡ እድሜውም እስከ 64 ዓመት ሊዘልቅ ይችላል፡፡

**ሐ. ሊዩተናንት ጄኔራል፡** ይህ ማዕረግ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ባለ ሦስት ኮከብ ከፍተኛ የጀኔራልነት ማዕረግ እርከን ነው፡፡ አንድ መኮንን ወደ ሌ/ጀኔራልነት ማዕረግ ከመድረሱ በፊት በጦር ኃይሎች ውስጥ በአመራር ከ 20 ዓመት ያልበለጠ አገልግሎት መስጠት አለበት፤ ከሜ/ ጀኔራል ማዕረግ ወደ ሌ/ጄነራል ማዕረግ ለመሸጋገር መሟላት ያለበት የአመራር ብቃቱ፣ በያዘው ማዕረግ የቆይታው ጊዜ፣ በወታደራዊ ሥነ-ምግባር ምንም አይነት ችግር የሌለበት፣ የአመራር የሥልጠና እርከኖችን ያለፈ፣ እና ክፍት የሥራ ቦታ መኖሩ ናቸው፡፡ ሌ/ጀኔራል ከሆነ በኋላ የሥራ ኃላፊነቱም የኮር ወይም የግንባር ወይም የህብረት የጥምር ጦር አዛዥ እና በሀገር መከላከያ ጠቅላይ መምሪያ፣ የመምሪያ መኮንን ሆኖ ማገልገል ነው፡፡ መኮንኑ በያዘው ማዕረግ ቢያንስ ሦስት ዓመት ማገልገል አለበት ነገር ግን በያዘው ማዕረግ አምስት ዓመት ከአገለገለ እና በጦር ሀይሎች ውስጥም 40 ዓመት ካገለገለ በጡረታ ይገለላል፤ የዕድሜ ጣሪያውም 62 ዓመት ይሆናል፡፡

**መ. ጀኔራል፡** ይህ ማዕረግ ከሌ/ጄነራል ቀጥሎ ከፊልድ ማርሻል ዝቅ ያለ ባለ አራት ኮከብ ማዕረግ ሲሆን በጦር ኃይሎች ማዕረግ አሰጣጥም ከፍተኛው የሹመት እርከን ነው፡፡ ከሌ/ጀኔራልነት ወደ ሙሉ ጀኔራልነት የማዕረግ እድገት ለመሸጋገር በቅድሚያ ክፍት የስራ ቦታ ሲኖር፣ በጦር ሀይሎች ውስጥም 20-23 ዓመት ያገለገለ፣ የአመራር ብቃት እና ልምዱ ስኬታማ የሆነ፣ በወታደራዊ ሥነ ምግባሩም ምንም ዓይነት እንከን የሌለበት፣ ለአመራርነት የሚሰጠውን ከፍተኛ የሳይንስና የጥበብ ሥልጠና እርከኖችን በተዋረድ የጨረሰ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሙሉ ጀኔራል የኋላፊነት ቦታም በጦር ኃይሎች ውስጥ የምድር ጦር ወይም የአየር ኃይል አዛዥ ወይም የህብረት ዕዝ አዛዥ ወይም የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ወይም የጦር ኃይሎች አዛዥ ሆኖ መሥራትን ያጠቃልላል፡፡ በያዘው ማዕረግ ቢያንስ አምስት ዓመት ያገለገለ ሆኖ በጦር ሀይሎች ውስጥ ያበረከተው የአገልግሎት ጣራ 40 ዓመት ከሞላ ጡረታ ይወጣል፡፡ የዕድሜ ጣሪያውም 64 ዓመት ይሆናል፡፡

የአንድ ሀገር የጦር ኃይል (የምድርኃይል፣ የአየር ኃይል፣ የባህር ኃይል) ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሦስት አይነት የአመራር ደረጃዎች ማለትም፡-

1. በቀጥተኛ የግንባር መስመር አመራር መኮንኖች
2. በከፍተኛ አመራር መኮንኖችና
3. በስትራቴጂክ አመራር መኮንኖች የተደራጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

በሰራዊቱ ውስጥ ጄነራል መኮንኖች የሆኑ ሁሉ የሥትራቴጂክ አመራር አካል ናቸው፡፡ አንድ መኮንን የብ/ጄነራል ማዕረግ ለመድረስ 22 ዓመት ማገልገል አለበት ከዚህ ውስጥ ከ7-8 ዓመታት ያለው ጊዜ የወታደራዊ የአመራር ጥበብ ሳይንስ የሚቀስምበት የዕውቀት ጉዞ መንገድ ነው፡፡

በአጠቃላይ የጄነራል መኮንኖች የወታደራዊ አመራር ጥበብ ሥልጠና መነሻው መሰረታዊ ከሆነው ከዕጩ መኮንንነት የሥልጠና እርከን ተነስቶ እስከ መጨረሻው የፖሊሲ እና ስትራቴጂ ትንተና ጥናት እና ምርምር ተቋም እስከ ሆነው የጦር ኮሌጅ ድረስ ይዘልቃል፡፡ የአመራር የሥልጠና እርከኖችን ያላለፈ ጄኔራል የተሟላ ተክለ ሰውነት እንደሌለው ይታሰባል ወይም ይቆጠራል፡፡

## 5. የቀድሞው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራሮች የሥልጠና ሂደት፤

በሀገራችን የመከላከያ ሠራዊት ታሪክ ውስጥ የወታደራዊ ትምህርትና ሥልጠና ከፍተኛ ቦታ እና ትኩረት ነበረው፡፡ በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የነበረው የመከላለከያ ሚኒስቴር ሁለት የጦር አካዳሚ ትምህርት ቤቶች ነበሩት፡፡ እነዚህም የሐረር ጦር አካዳሚና የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በትንሽ ዓመት ቆይታ የተቋቋመ በርካታ ብርቅዬ የጦር መኮንኖችን በጥራት ያስመረቀ ተቋም ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ከ1ኛ ኮርስ እስከ 54ኛ ኮርስ ድረስ መኮንኖችን ያስመረቀ ቢሆንም በደርግ ጊዜ በነበረው የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የማሰልጠን ሥራውን ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ማካሄድ ተስኖት ነበር፡፡

የሐረር ጦር አካዳሚ እ.ኤ.አ 1957 ከተቋቋመ አንስቶ እስከ ተዘጋበት 1977 ድረስ በርካታ መኮንኖችን አስመርቋል። አካዳሚው ለጎረቤት ሀገሮች ጭምር መኮንኖችን ያሰለጥን ነበር፤ ሁለቱም የጦር ትምህርት ቤቶች አለም ዓቀፍ የአመራር ስልጠና መመዘኛ ስታንዳርድን በጠበቀ መልኩ ተደራጅተው ብዙ አመራሮችን አሰልጥነው በማስመረቅ ለሃገሪቱ አበርክተዋል፡፡ ከእነዚህ የጦር አካዳሚ ት/ቤቶች ከተመረቁ መኮንኖች ውስጥ ከምክትል መቶ አለቃነት  እስከ ሌ/ጀኔራልነት ማዕረግ የደረሱ ይገኙበታል፡፡እነዚህ ጄኔራል መኮንኖች በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ የተካኑና በሥነምግባር የታነፁ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የተማሩ ከፍተኛ ብቃት እና ችሎታ ያላቸው ሀገራቸውን በወታደራዊ መስክ ያስጠሩ ብርቅዬ የኢትዮጵያ የሀገር መመኪያ ልጆች ነበሩ፡፡ የሐረር ጦር አካዳሚ  ከ1ኛ ኮርስ እስከ 21ኛ ኮርስ ድረስ በማስተማር አስመርቋል፡፡

በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ጦር ኃይሎች የመከላከያ ሥልጠና ፖሊሲ በሚያዘው መሠረት ወታደራዊ የአመራር ጥበብና ሳይንስ በተገቢው ሁኔታ ከዕጩ መኮንን ሥልጠና እስከ ስታፍ ኮሌጅ ድረስ የዘለቁ 293 ጄነራል መኮንኖች ነበሩት(ሰንጠረዥ-ለን ይመልከቱ)።

**ሰንጠረዥ–ለ፡- በሦስቱም መንግሥታት የተሾሙ ጄነራል መኮንኖች (1927–2007 ዓ/ም)**

| ተ.ቁ | የማዕረግ ደረጃ | ከ1927 እስከ 1983 | | ከ1983 ጀምሮ | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አፄ ኃይለ ሥላሴ | ደርግ | ህወሓት/ ኢህአዴግ | |
| 1 | ጄኔራል | 0 | 0 | 1 | 1 |
| 2 | ሌ/ጄኔራል | 15 | 3 | 6 | 24 |
| 3 | ሜ/ጄኔራል | 6 | 32 | 24 | 62 |
| 4 | ብ/ጄኔራል | 63 | 174 | 99 | 336 |
| ጠቅላላ ድምር | | 84 | 209 | 130 | 423 |

በአጠቃላይ እነዚህ ጄኔራል መኮንኖች በዚህ ጽሁፍ ዋና አካል ላይ የተቀመጡትን የወታደራዊ አመራር ሥልጠና እርከኖች ይዘት እና ሂደት አሟልተው የተመረቁና በተግባር በጦር ሜዳ ውሎአቸውም አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ እንደነበሩ ድርሳናቸው ያስረዳል፡፡


## 6. የአሁኑ  የሀገር መከላከያ መኮንኖች ከወታደራዊ አመራር ሳይንስና ጥበብ አንፃር

የዛሬው የሕወሓት ሰራዊት ከሽምቅ ተዋጊነት በቀጥታ መደበኛ የሀገሪቱ ሠራዊት እንዲሆን በምድር ሀይልና በአየር ሀይል ተከፋፍሎ እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን ሠራዊቱን እንዲመሩ የተመደቡት የበታች ሹሞችና መኮንኖች በሙሉ በምንም ዓይነት ወታደራዊ የአመራር ስልጠና ውስጥ ሳያልፉና ከወታደራዊ ሙያ ሳይንስና ሕግጋት ውጭ በዘርና በፖለቲካ ወገንተኝነት ላይ በመመሥረት ማዕረግ በጅምላ የተሰጣቸው ናቸው:: ይህ ደግሞ በሀገሪቷ መጥፎ የታሪክ ጠባሳ እየጣለ ይገኛል።

በወታደራዊ የአመራር ስልጠና ታሪክ ያለምንም የአመራር ስልጠና የጄነራል መኮንነት ማዕረግ የሰጠች የመጀመሪያ አፍሪካዊት አገር ኢትዮጵያ ነች:: ሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ከ1983 ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ ለ130 አባሎቹ (ለዝርዝሩ አባሪ ፩ን ይመልከቱ) የጄኔራል መኮንነት ማዕረግ የሰጠ ሲሆን 97 በመቶ የሚሆኑት ተሿሚዎችም በምንም ዓይነት የወታደራዊ አመራር ሳይንስና ጥበብ ስልጠና ውስጥ ያላለፉ ናቸው። ወደ 52 በመቶ (67ቱ) የጄኔራል መኮንንነት ቦታም የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የህወሓት አባላት ተቆጣጥረውታል (ሰንጠረዥ-ሐን እና ሥዕል-አንድን ይመልከቱ)::

**ሰንጠረዥ-ሐ፦ ጄነራል መኮንኖች በብሄረሰብ ስብጥራቸው**

| ብሔረሰብ | የተለያዩ የጀነራልነት ማዕረጎች | | | | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጄነራል | ሌትናት ጄነራል | ሜጀር ጄነራል | ብርጋዲየር ጄነራል | |
| ትግራይ | 1 | 4 | 15 | 47 | 67 |
| አማራ | 0 | 0 | 5 | 27 | 32 |
| ኦሮሞ | 0 | 1 | 3 | 20 | 24 |
| አገው | 0 | 1 | 1 | 1 | 3 |
| ደቡብ ሕዝቦች | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 |
| ቅይጥ ብሄሮች | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 |
| | | | | **አጠቃላይ ድምር** | **130** |




በአጠቃላይ ከላይ በሥዕሉና በሠንጠረዡ እንደተመለከትነው፤ ሂደቱ የሀገሪቱን የወታደራዊ ስልጠና ገጽታን ከማበላሸቱም በላይ መጥፎ የታሪክ ጠባሳ እየጣለ ይገኛል:: በሚገርም ሁኔታ የሀገር መከላከያ የስትራቴጂክ አመራር እንዲሰጡ በህዋሓት የተሾሙ ጄነራል መኮንኖች መሰረታዊ የሆነውን የአመራር ስልጠና እንኳን ያልወሰዱ እና የአካዳሚክስ እውቀታቸው በጣም ዝቅተኛና በአብዛኛው ከ5ኛና ከ9ኛ ክፍል ያላለፈ መሆኑን የግል ሕይወት ታሪካቸው ያሳያል።

አንድን ሠራዊት ለመምራትም ሆነ ለማሰልጠን ቀድሞ ስልጥኖ መገኘት ጥያቄ ውስጥ ሊገባና ሊጣስ የማይችል መርህ ነው:: የህወሓት መንግስት ከፈጸመው አስከፊ ወንጀል አንዱ ምንም ዓይነት የወታደራዊ አመራር ትምህርትና ስልጠና ሳያገኙ ጄነራል ብሎ በመሰዬም ሠራዊት እንዲመሩ ማድረጉ ነው:: የአሁኑ ጄኔራል መኮንኖች በአካዳሚክስም ሆነ በወታደራዊ ሳይንስና የአመራር ጥበብ ድህነት የተጎዱ፣ ጫካ በነበሩበት ወቅት መደበኛ ባልሆነ የሽምቅ ውጊያ ዕውቀት ብቻ ተኮፍሰው የኖሩ አሁንም በዚያው መንገድ የሚጓዙ ናቸው::

የህወሓት ጄነራል መኮንኖች ስለወታደራዊ አመራር ጥበብ ስልጠና ምንነትና ይዘት እንዲሁም ሂደት ምን እንደሆነ ግንዛቤ የሌላቸውና የማወቅ ፍላጎት የሌላቸው ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት በአስተርጓሚ እንዲማሩ ተሞክሮ ነገር ግን ሳይሳካ መቅረቱ በተጨባጭ የሚታወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም "አሁን እኛ ጄነራል መኮንኖች ስለሆንን አንማርም ምን ያደርግልናል" በሚል ነበር። በአሁኑ ወቅት ሠራዊቱ እየተመራ ያለው በእነዚህ ዓይነት ሰዎች ነው! የሚገያስርመው ነገር በሚመሩት ሰራዊት ወስጥ የሚገኙ የመካከለኛ እና የዝቅተኛ አመራር መኮንኖች በወታደራዊ የአመራር ስልጠና ንድፈ ሀሳብም (Theory) ሆነ ተግባራዊ ስራዎች አለቆቻቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ይበልጧቸዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እድሉ ቢሰጣቸው እነዚህን ጄኔራሎች በብቃት መልሰው ሊመሯቸው የሚችሉ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የወታደራዊ ሳይንስ ንድፈ ሀሳብ (theory) እንደሚያሳየው አንድ ወታደር መኮንን የሚባለው የአመራር ጥበብ በመውሰድ በተገቢ ሁኔታ ካጠናቀቀ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ንድፈ ሀሳብ አንፃር ለህወሓት ጄነራል መኮንኖች ምን ስም ቢሰጣቸው ይመጥናቸዋል? የበታች ሹም ቢባሉ፣ ለበታች ሹምነት ማዕረግ የሚያበቃውን የአመራር ስልጠና አልወሰዱም፡፡ ከበታች ሹም ቀጥሎ ወደታች ያለው ማዕረግ ቢሰጣቸው ደግሞ እሱንም እንኳን ለማሟላት መደበኛ የሆነውን መሠረታዊ የወታደራዊ ስልጠናም አልወሰዱም፡፡ በዚህ ነባራዊ ሐቅ በመንተራስ ከተራ ወታደር በስተቀር ሊሰጣቸው የሚችል ምንም ዓይነት መጠሪያ ስም የለም፡፡ ሕወሓቶች ጫካ እያሉም ሆነ አሁን የሚጠራሩበት "ተጋዳላይ እከሌ" "ወዲ እከሌ" የሚለው መጠራሪያቸው የሚመጥናቸው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ ሌ/ጄነራል ብለው የሾሙትን ከፍተኛ መኮንን ወዲ ወረዳ እያሉ ይጠራሉ፡፡ ይህ ባጠቃላይ ሲታይ ሠራዊቱ የአንድ መደበኛ ሠራዊት አካልነት ባህሪም ሆነ ተግባር አይታይበትም።

የህወሓት ጄኔራል መኮንኖች የወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ፣ ዕውቀትና አመራር አናሳና ደካማነት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በተጨባጭ በግልጽ የተከሰተበት የታሪክ አጋጣሚ ታይቶ አልፏል:: ይህ ጦርነት እልፍ አዕላፍ የሆኑ የደሃው ኢትዮጵያዊውያን/ት ልጆች ህይወት የተቀጠፈበትና የሀገሪቷ አንጡራ ሀብት የወደመበት አስከፊ ጦርነት ነበር:: ለዚህ ደግሞ ተጠያቂዎቹ:-

1ኛ፡ የሕወሓት ከፍተኛው አመራር እና

2ኛ፡ የህወሐት ስትራቴጂክ አመራር ሰጭ ጄኔራሎች ናቸው

ከላይ የተጠቀሱት የሕወሓት ጄኔራል መኮንኖች የወታደራዊ ትምህርትና ስልጠና ሳይወስዱ ወይንም ሳይቀስሙ ሠራዊቱን እንዲመሩ በመደረጋቸው ከፍተኛ ጉዳትና አደጋ ደርሷል:: ይህ ሁኔታ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥ መኪና ያለሙብራት መንዳት ወይም መኪናን ያለመሪ ለመንዳት እንደሚደረግ ሙከራ ያህል ይቆጠራል::

በአጠቃላይ የመኮንኖች የወታደራዊ አመራር ጥበብ ሥልጠና ምንነትና ይዘት እንዲሁም ሂደቱን እና የመኮንኖች የማዕረግ ዕድገት አሰጣጥ መነሻውም ሆነ መድረሻው የወታደራዊ ትምህርትና ስልጠና መሆኑን በሚገባ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር አይተናል፡፡

## 2. ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአጠቃላይ የወታደራዊ ትምህርት እና ስልጠና ይዘትና ሂደት ምን እንደሚመስልና አሁን ያለውን የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሚመሩትን ጄኔራል መኮንኖችን ዓለም ከደረሰበትና ተቀባይነት ካለው የወታደራዊ ትምህርትና ስልጠና ስታንዳርድ እንፃር የሙያ ብቃት ደረጃቸውን በመመዘንና በመተንተን በጥልቀት ለመዳሰስ ሙከራ አደርጓል። የወታደራዊ ሳይንስና የአመራር ጥበብ ሥልጠና በተዋረድ ከመሰረታዊ ሥልጠና ወደ ቀጣዩ ስልጠና እንዴት እንደሚሸጋገርና እንደሚገባ፣ ሥልጠናው የሚያካትታቸው የትምህርት ዓይነቶች ፣ ከሥልጠናም በኋላም በኃላፊነት ሊመሩት የሚችሉት ኃይልና የወታደር ብዛት፣ የሥልጠናው የቆይታ ጊዜ፣ እንዲሁም ሥልጠናውን ሲጨርሱ የሚሰጠው የትምህርት ማስረጃ እና ከተወሰነ አገልግሎት በኋላ ከአንዱ የአመራር ሥልጠና ወደ ሌላው የአመራር ሥልጠና እርከን እንዴት እንደሚሸጋገሩ ሥዕላዊ በሆነ መለኩ በማቅረብ ሳይንሳዊ የሆነ የአመራር ሥልጠና ሂደት ዋነኛው እና ትልቁ መንገድ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አንድ ጀኔራል መኮንን በሚያዝዘው ኃይል ውሰጥ ለየእርከኑ አመራር ሰጭ ሊሆኑ የሚገባቸውን ማዕረጋቸውን፣ የኃላፊነት ቦታና ሠራዊቱ የሚዋጋበትን የጦርነት ህግ፣ ሰራዊቱ የሚሰለጥንበትን የስልጠና ፖሊሲ፣ የወታደራዊ ዶክትሪንና ስትራቴጂ መቅረጽ መቻል ያለበት መሆኑን ያስረዳል:: አሁን መሬት ላይ ያለው ሐቅ የሚያሳየው ግን ተሿሚዎቹ ከህሎቱ እና ችሎታው የሌላቸው በመሆኑ ከላይ የተዘረዘሩትን አንድ ብቃቱ የተረጋገጠለት ጀኔራል መኮንን ሊፈፅማቸው የሚገባ ተግባራት በብቃት ማከናወን እንደማይችሉ ጥናቱ ያስረዳል:: የእነሱ ዶክትሪንና ስትራቴጂ ቀረጻ መሬት ወረራ ፣ ዝርፊያ፣ ምዝበራ፣ አፈናና ዜጎችን በውጭ ሀገራት ሳይቀር እንዴት መጥለፍ እንደሚቻል ያተኮረ ላቅ ያለ ተንኮል ብቻ ነው:: በአንድ ወቅት ሟች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጄነራል መኮንኖቹን ሲገመግሙ ያስቀመጡትን ድምዳሜ በመጥቀስ ፅሁፍን እናበቃለን። “እናንተ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴም ሆነ በደርግ ዘመነ መንግስት ከነበሩት ጄኔራል መኮንኖች ጋር ስትነፃጸሩ የሰማይና የምድር ያህል ትራራቃላችሁ:: የእናንተ ችሎታ አንድ ሻለቃ ወይም 400 መቶ ሰው ያለው ሀይል ከማዘዝ ያለፈ አይደለም!’’

በመጨረሻም ከዚህ በታች በተቀመጠው አባሪ ሰነድ ሰንጠረዥ ፩፣ ሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ከ1983 ዓ.ም. አንስቶ እስካሁን ድረስ የጦር ኃይሉ የተዋቀረው በአንድ ብሔር (በትግራይተወላጆች) የበላይነት፣ ያለአንዳች የወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ

ሥልጠና መሆኑን ማንም ሊያስተባብለው በማይችል መልኩ ጥሬ ሐቁ ተቀምጧል። ይህ በራሱ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ለምን በዚህ አሳዛኝ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የማኅበረሰባዊ ዝቅጠት ላይ እንደምትገኝ ቁልጭ አድርገው ከሚያሳዩት ተግዳሮቶች (Factors) አንዱ ሊሆን ይችላል።

## 3. አባሪ ሰነድ- ፩ (Annex-1)

| የኢህአዴግ ድኅረ 1983 ዓ.ም. የወታደራዊ ማዕረግ በብሔር ተዋፅዖ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ወቅታዊ ሁኔታ | ብሔር | የ ሳይ |
| 1 | ሳሞራ የኑስ | ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ (በከፊል) | የለም |
| 2 | ፃድቃን ገብረትንሣኤ | ሌ/ጄኔራል | የተባረሩ | ትግሬ | የለም |
| 3 | አበባው ታደሰ | ሌ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አገው | የለም |
| 4 | ታደሰ ወረደ | ሌ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 5 | ሰዓረ መኮንን | ሌ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 6 | ባጫ ደበሌ | ሌ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ኦሮሞ | የለም |
| 7 | ዮሐንስ ገብረመስቀል | ሌ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 8 | አበበ ተክለሃይማኖት | ሜ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 9 | ገዛኢ አበራ | ሜ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 10 | አለምሸት ደግፌ | ሜ/ጄኔራል | የተባረሩ | ኦሮሞ | በወ ሳይን የሰለ |
| 11 | ኃይሌ ጥላሁን | ሜ/ጄኔራል | የተባረሩ | አማራ | የለም |
| 12 | ገብረእግዚአብሔር መብራህቱ | ሜ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 13 | ስዩም ሐጎስ | ሜ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አገው | የለም |
| 14 | አለሙ አየለ | ሜ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አማራ | የለም |
| 15 | ኃየሎም አርአያ | ሜ/ጄኔራል | የተገደሉ | ትግሬ | የለም |
| 16 | ብርሃነ ነጋሽ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 17 | አብርሃ ወልደማርያም | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 18 | ሞላ ኃይለማርያም | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 19 | አደም መሐመድ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 20 | ብርሃኑ ጁይላ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 21 | ገብራት አየለ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ኢብራሂም አብዱልጀሊል | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 23 | ፍሥሐ ኪዳነ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 24 | ተስፋይ ግደይ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 25 | መሐሪ ዘውዴ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 26 | ሐሰን ኢብራሂም | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 27 | መለሰ በለጠ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 28 | ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 29 | ገብረ አድሃና | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 30 | ማሞ ግርማይ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 31 | አባዱላ ገመዳ | ሜ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 32 | የማነ ገብረኪዳን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 33 | አበራ ተክለዮሐንስ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 34 | ጌታቸው ሺጠራው | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 35 | አደፍርስ ደነቀ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አማራ | በወታ<br>ሳይን<br>የሰለ |
| 36 | ነጋሽ ዳኘው | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 37 | በርሄ ተስፋዬ ሐጎስ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 38 | ንጉሴ ለማ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 39 | ዘውዱ እሸቴ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | በወታ<br>ሳይን<br>የሰለ |
| 40 | መሐመድ ኢሻ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 41 | ምስጋናው አለሙ | ብ/ጄኔራል | Active | አማራ | የለም |
| 42 | ከንፈ ዳኘው | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 43 | ገብረሚካኤል በየነ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 44 | አከለ አሳየ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 45 | ህንፃ ወልሰጊዮርጊስ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 46 | ተከለብርሃን ካህሳይ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 47 | ጌታቸው ጊዲና | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 48 | ማዕሾ በየነ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 49 | ወንድወሰን ተካ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 50 | በየነ ስዩም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 51 | አታክልቲ በርሄ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 52 | ጉዕሽ ፅጌ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 53 | ገብረኪዳን ገብረማርያም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 54 | ማዕሾ ሐጎስ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 55 | ገብሩ ገብረሚካኤል | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 56 | መሸሻ ገብረሚካኤል | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 57 | አብርሃ አረጋይ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 58 | ደግፌ ቢዲ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | የደቡብ ሕዝብ ብሄር ብሔረሰቦች | የለም |
| 59 | አስካለ ብርሃን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 60 | ኃለፎም እጅጉ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 61 | ሃለፎም አለሙ (ቼንቶ) | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የሐረ<br>ተቋ |
| 62 | አብረሃ ተስፋዬ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 63 | ሙሉ ግርማይ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 64 | ወልደገብርኤል ባቢ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 65 | ፍሥሐ ኪዳነማርያም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 66 | አሰፋ ገብሩ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 67 | የማነ ሙሉ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 68 | ገብረመድህን ፈቃዱ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 70 | አሥራት ዶኖይሮ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ቅይጥ | የለም |
| 71 | ጥጋቡ ይልማ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 72 | ዘውዱ በላይ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 73 | ኩምሳ ሻንኃ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 74 | አቻሉ ሽለመ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 75 | ሹማ አብደታ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 76 | ድሪባ መኮንን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | የደቡብ ሕዝብ ብሄር ብሔረሰቦች | የለም |
| 77 | ከድር አራርሳ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 78 | ይብራህ ዘሪሁን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 79 | ኩመራ ነጋሩ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 80 | ዱባለ አብዲ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 81 | ምግበ ኃይለ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 82 | ተከላይ አሸብር | ብ/ጄኔራል | የተባረሩ | ትግሬ | የለም |
| 83 | አብራሃ መጅሙ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 84 | ውዲ ሮማን | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ኤርትራዊ | የለም |
| 85 | ከማል ገልቹ | ብ/ጄኔራል | ሥርዓቱን የከዱ | ኦሮሞ | የለም |
| 86 | ኃይሉ ጎንፋ | ብ/ጄኔራል | ሥርዓቱን የከዱ | ኦሮሞ | የለም |
| 87 | ሰይፉ በቀለ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አማ | በወ… ሳይን… የሰለ… |
| 88 | ደምሴ ጎሹ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አማራ | በወ… ሳይን… የሰለ… |
| 89 | ደምስ ጎሹ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | አማራ | የለም |
| 90 | ኩመር አስፋው | ብ/ጄኔራል | የተባረሩ | ኦሮሞ | የለም |
| 91 | አብዱራህማን እስማኤል | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 92 | ዘነበ አማረ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 93 | ዜናዊ ገብረእግዚአብሔር | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 94 | ምዑዘይ መኮንን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 95 | ገብረእግዝኤበሔር መኮንን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 96 | መሐመድ ተሰማ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 97 | እንዳልካቸው ወልደኪዳን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 98 | ኢተፋ ረጋ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 99 | ሃብታሙ ጥላሁን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 100 | ጀማል መሐመድ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 101 | ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 102 | ዋኘው አመረ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 103 | አሰፋ ቸኮል | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 104 | አመረ ገብረሃይሉ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 105 | በላይ ስዩም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 106 | ደሳለኝ ተሾመ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 107 | አብዱ ከድር | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 108 | ሙላቱ ጀልዱ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 109 | ጥጋቡ ፍትሕ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 110 | ተስፋይ ወልደማርያም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 111 | ታደሰ አመለ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 112 | ከፍያለው አመዴ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 113 | አህመድ ሀምዛ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 114 | አዳምነህ መንግሥቴ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 115 | ዘውዱ ኪሮስ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 116 | መሰለ መሠረት | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አማራ | የለም |
| 117 | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 118 | ጠና ኩሩንዲ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ኦሮሞ | የለም |
| 119 | በለጠ ምሳሌ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 120 | ታደሰ ጉዋና | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 121 | ተፈራ ማሞ | ብ/ጄኔራል | ወህኒ የወረዱ | አማራ | የለም |
| 122 | አሳምነው ፅጌ | ብ/ጄኔራል | ወህኒ የወረዱ | አማራ | የስታ<br>ምሩ |
| 123 | መስፍን አማረ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ትግሬ | የለም |
| 124 | አቤል አየለ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 125 | የምር መኮንን | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | አገው | የለም |
| 126 | በርሄ ገብረማርያም | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 127 | ፍሥሐ በየነ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 128 | ሙሉጌታ በርሄ | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 129 | ኃይለሥላሴ እምበት | ብ/ጄኔራል | በማገልገል ላይ | ትግሬ | የለም |
| 130 | አሳምነው በዳኔ | ብ/ጄኔራል | በጡረታ የተገለሉ | ቅይጥ | በወ<br>ላይን<br>የሰለ |

| EPRDF's Post 1991 Military Leadership Rank and Ethnicity Distribut | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Militar and Ar** |
| 1 | Samora Yenus | General | Active | Part Tigre | None |
| 2 | Tsadkan Gebretensae | Lieutenant General | Fired | Tigre | None |
| 3 | Abebaw Tadesse | Lieutenant General | Active | Agew | None |
| 4 | Tadess Worede | Lieutenant General | Retired | Tigre | None |
| 5 | Se'are Mekonnen | Lieutenant General | Active | Tigre | None |
| 6 | Bacha Debele | Lieutenant General | Retired | Oromo | None |
| 7 | Yohannes Gebremeskel | Lieutenant General | Active | Tigre | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | Abebe Teklehamanot | Major General | Fired | Tigre | None |
| 9 | Gezae Abera | Major General | Retired | Tigre | None |
| 10 | Alemshet Degefe | Major General | Fired | Oromo | Military Sci trained |
| 11 | Haile Tilahun | Major General | Fired | Amhara | None |
| 12 | Gebregziabher Mebrahtu | Major General | Retired | Tigre | None |
| 13 | Seyoum Hagos | Major General | Retired | Agew | None |
| 14 | Alemu Ayele | Major General | Retired | Amhara | None |
| 15 | Hayalom Araya | Major General | Deceased | Tigre | None |
| 16 | Berhane Megash | Major General | Active | Tigre | None |
| 17 | Abrha Woldemariam | Major General | Active | Tigre | None |
| 18 | Molla Hailemariam | Major General | Active | Tigre | None |
| 19 | Adem Mohammed | Major General | Active | Tigre | None |
| 20 | Birhanu Juila | Major General | Active | Oromo | None |
| 21 | Gebrat Ayele | Major General | Active | Tigre | None |
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Military and Art** |
| 22 | Ibrahim Abduljelil | Major General | Active | Tigre | None |
| 23 | Fisha kidana | Major General | Active | Tigre | None |
| 24 | Tesfay Giday | Major General | Active | Tigre | None |
| 25 | Mehari Zewdien | Major General | Active | Tigre | None |
| 26 | Hassan Ibrahim | Major General | Active | Amhara | None |
| 27 | Melese Beleate | Major General | Active | Amhara | None |
| 28 | Yohannes Woldegiorgis | Major General | Active | Tigre | None |
| 29 | Gebre Adhana | Major General | Active | Tigre | None |
| 30 | Mamo Girmay | Major General | Active | Amhara | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 31 | Abadula Gemeda | Major General | Active | Oromo | None |
| 32 | Yamane Gebrekidan | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 33 | Abera Tekleyohanis | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 34 | Getachew Shiteraw | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 35 | Adefris Deneke | Brigadier General | Retired | Amhara | Military Sci trained |
| 36 | Negash Dagnew | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 37 | Berha Tesfaye Hagos | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 38 | Nigussie Lemma | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 39 | Zewdu Eshete | Brigadier General | Active | Amhara | Military Sci Trained/Ho |
| 40 | Mohamod Isha | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 41 | Misganaw Alemu | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 42 | Kinfe Dagnew | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 43 | Gebremichael Beyne | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 44 | Akele Assaye | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 45 | Hintsa Woldegiorgis | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Military and Art** |
| 46 | Taklebirhan Kahsay | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 47 | Getachew Gidina | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 48 | Masho Beyene | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 49 | Wondwosen Teka | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 50 | Beyne Seyoum | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 51 | Alaklti Berhe | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 52 | Guesh Tsige | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 53 | Gebrekidan Gebremariam | Brigadier General | Active | Tigre | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 54 | Maesho Hagos | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 55 | Gebru Gebremichael | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 56 | Mashesha Gebremichael | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 57 | Abreha Aregay | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 58 | Degife Bidi | Brigadier General | Active | SNNP | None |
| 59 | Askale Berhan | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 60 | Halefom Ejigu | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 61 | Halefom Alemu (chento) | Brigadier General | Active | Tigre | Harrar Mili Acadamy G |
| 62 | Abreha Tesfaye | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 63 | Mulu Germai | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 64 | Woldegabriel Babi | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 65 | Feseha Kidanemariam | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 66 | Assefa Gebru | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 67 | Yemane Mulu | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 68 | Gebremedhin Fekadu | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Military and Art T** |
| 69 | Tarekegn Kassahun | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 70 | Asrat Donoyro | Brigadier General | Active | Mixed | None |
| 71 | Tigabu Yilma | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 72 | Zewdu Belay | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 73 | Kumsa Shango | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 74 | Achalu Sheleme | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 75 | Shuma Abdeta | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 76 | Driba Mekonnen | Brigadier General | Active | SNNP | None |
| 77 | [illegible] | Brigadier General | Active | [illegible] | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 78 | Yebrah Zerihun | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 79 | Kumera Negaru | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 80 | Dubale Abdi | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 81 | Mgbe Haile | Brigadier General | Retired | Tigre | None |
| 82 | Teklai Ashebr | Brigadier General | Fired | Tigre | None |
| 83 | Abraha Mejmooe | Brigadier General | Retired | Tigre | None |
| 84 | Wedi Roman | Brigadier General | Retired | Eritrean | None |
| 85 | Kemal Gelchu | Brigadier General | Defected | Oromo | None |
| 86 | Hailu Gonfa | Brigadier General | Defected | Oromo | None |
| 87 | Seifu Bekele | Brigadier General | Retired | Amhara | Military Sci trained |
| 88 | Demissie Goshu | Brigadier General | Retired | Amhara | Military Sci trained |
| 89 | Demis Gushu | Brigadier General | Retired | Amhara | None |
| 90 | Kumer Asfaw | Brigadier General | Fired | Oromo | None |
| 91 | Abdurahman Ismael | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 92 | Zenebe Amare | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Military and Art T** |
| 93 | Zenawi Gebregziabbher | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 94 | Muzey Mekonen | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 95 | Gebregziobher Beyene | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 96 | Mohammed Tessema | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 97 | Endalkachew Weldekidan | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 98 | Itafa Rega | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 99 | Habtamu Tilahun | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 100 | Jemal Mohammed | Brigadier General | Active | Tigre | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 101 | Gebregzibaher | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 102 | Wagnew Amere | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 103 | Assefa Chekol | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 104 | Amere Gebrehailu | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 105 | Belay Seyoum | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 106 | Desalegne Teshome | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 107 | Abdu Kedir | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 108 | Mulatu Jeldu | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 109 | Tigabu Fethe | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 110 | Tesfay Weldemariam | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 111 | Tadesse Amelo | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 112 | Kefeyalew Amede | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 113 | Ahmed Hamza | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 114 | Adamneh Mengestie | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 115 | Zewdu Kiros | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| **No** | **Full Name** | **Rank** | **Status** | **Ethnicity** | **Military and Art** |
| 116 | Mesele Meseret | Brigadier General | Active | Amhara | None |
| 117 | Solomon Itefe | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 118 | Tena Kurundi | Brigadier General | Active | Oromo | None |
| 119 | Belete Misale | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 120 | Tadesse Guana | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 121 | Tefera Mamo | Brigadier General | Imprisoned | Amhara | None |
| 122 | Asamnew Tsigie | Brigadier General | Imprisoned | Amhara | Staff Colleg |
| 123 | Mesfin Amare | Brigadier General | Retired | Tigre | None |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 125 | Yemer Mekonnen | Brigadier General | Active | Agew | None |
| 126 | Berhe Gebremariam | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 127 | Fissiha Beyene | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 128 | Mulugeta Berghae | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 129 | Haileselassie Embet | Brigadier General | Active | Tigre | None |
| 130 | Asamnew Bedani | Brigadier General | Retired | Mixed | Military trained |